## የናት ቀን

የናት ቀን ደረሰ ካርድ እንግዛ ወጥተን

ስጦታ እናፈላልግ ከረሜላም ቢሆን፤

ደስ ይበልሽ እንበል እማማን አቅፈናት

ብዙም አያቆየን የዕለት በአሏ ናት፡፡

አነስተኛ ልጆች እናንተም በሳሉ

ቆዩ አትጣደፉ እስቲ ዝግ በሉ።

እናት የዘላለም ያይደለች ያንድ ቀን

ፍቅር የማያጥራት ወራት ዓመታቱን፣

ለልጆችዋ ሥጋት ሆነውም ሙሉ ሰው

ከስሜትዋ አይርቁ ሁሌም ተጎዱ ነው፡፡

ስድሳ ሰባ ገብታ መድከሟም ሲጨመር

ሲያባንናት አለ የልጆችዋ ነገር፡፡

ልብ በሉ አድምጡ የናት ቀን ሲወሳ

ባንድ ቀን አያልቅም የናት ዋጋ ካሳ፡፡

ዓመቱን የሚዘልቅ ፍቅር፣ ድጋፍ ሰጥቶ፤

ይገባል ሊያስቧት ታች ወርዶ ላይ ወጥቶ፡፡

እናቶች ከልጆቻችሁ ጋር ያሳለፋችሁት

የናት ቀን ሁላችሁንም በደስታ መንፈስ ያበ

ለጸገና ያቀራረበ በየእለቱም እዚህ አቋም ላይ

ያተኮረ እንዲሆን የመድኃኔዓለም ፈቃዱ ይሁን፡፡

ከንፈ ገበየሁ ዶር

## ያገር ቀን

አገርም እናት ናት ብዙ ሚባልላት

ቀይ ጥቁር አፍርታ ሳትል ወንድና ሴት

ጥቂቱ በደጋ ከፊሉ በቆላ

አምላክ ያደላትን ለኑሮ አስተካከላ

ከተማ እንዲከትም አስተምራ መላ

በውቀትም ልጆችዋ እንዳይቀሩ ኋላ።

ተባብረው ገፊውን ደጋግመው መክተው

ኢትዮጵያዊነትን ጀግኖችዋ አቆይተው;

እንዲህ ወደኋላ እኔነት ፈንጥቆ

የኢትዮጵያን ውበቷን ትብብሯን ንቆ;

አይበጅም ለሁሉም ይህ ምሪት አይጠቅምም

ሙቶ ሃያ ሚልዮን አያስተቃቅፍም፡፡

ማስተቃቀፍ ማለት ሰፊ ነው ትርጉሙ

መጎዳዳት ጠፍቶ ንብረት ላይ አቋሙ;

ስልጣን ሃይል አግኝቶ ፍርድ ወርዶ ተሰምቶ

ቋንቋ ብሄር ሳይል ሰው እንደሰው ታይቶ

ተከብሮና ታፍሮ የትም ሄዶ ሠርቶ

እንደየችሎታው ለልማት አዋጥቶ

ባገኘውም እውቀት ሌሎችንም ረድቶ

ይቺ ናት ኢትዮጵያ ህዝቧን ያፋቀረች

ተከብራም ተፈርታ ልጆችዋን ያስማማች፡፡

አሁንም አልመሸም ትኩረቱን ከሰጠን

ባንድ ሆነን ልናከብር እውነት የኢትዮጵያን ቀን፡፡